# ኢትዮጵያዊያንና አሜሪካዊያን ለፍትሕና ለዴሞክራሲ
# ሎስ አንጀለስ

## ማሳሰቢያ ለወያኔ ህወሃት አገልጋዮችና አጫፋሪዎች

ሀገር በህወሃት (የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር) ጠባቦች እየተቆራረጠና ወገን በረሃብ አለንጋ ተቀጥቶ እያለቀ፤ በቁራጭ መሬትና በትናንሽ ጥቅሞች ተደልላችሁ በወገኖቻችን ላይ የመከራ ዘመናቸውን የምታራዝሙ ሁሉ ከዚህ ተግባራችሁ እንድትቆጠቡ እንጠይቃችኋለን። ዛሬ ዘረኛውና አምባገነን መንግሥት በወገኖቻችንና በሀገራችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ገሀድ በደል የዓለም ኅብረተሰብ እያወገዘው እናንተ ግን ለጠባብ ብሄርተኞች አጎብድዳችሁ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በወገናችሁ ላይ በጠላትነት መቆማችሁ በሀገርና በወገን ላይ ከፍተኛ በደል እየፈጸማችሁ መሆኑን መረዳት አለባችሁ።

በየትም ሀገር ቢሆን ለሀገርና ለወገን ጠላት መጠለያና ድጋፍ የሰጠ ሁሉ ከከሃዲ ባንዳ ተለይቶ አይታይም። በሕዝባችን ላይ ህወሃት ለሚያደርሰው በደል ሁሉ እናንተም ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ እንደሆናችሁ ማወቅ ይኖርባችኋል። በረሃብ ለሚያልቀው፤ በጦርነት ለሚሞተውና ለሚጎዳው፤ ለውጭ ከበርቴ ከወገን ደሃ ገበሬው ተነጥቆ ለሚሰጠው ለም መሬት፤ በየጊዜው በህወሃት ለሚገደለውና ለሚታሠረው አርበኛ ሁሉ፤ ወያኔ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወገን ለሚዘርፈው ገንዘብ ሁሉ አስፈጻሚ በመሆናችሁ ምንጊዜም ቢሆን ይዘግይ እንጂ ከተጠያቂነት አትድኑም። እኛም በነፃነት ጊዜ በገባችሁበት ገብተን እናጋልጣችኋለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክም ይፋረዳችኋል።

የወያኔ ህወሃት ሥርዓት ተንኮታክቶ እንደሚወድቅ የሚያጠያይቅ አይደለም። በቅርቡ በሰሜን አፍሪካና በዓረብ ሀገሮች እንደዚሁም በዓለም ዙሪያ በየጊዜው የተከሰቱ አምባገነንና ዘረኛ መንግሥታት በሙሉ እንደዚሁ መጨረሻቸው እጅግ አስከፊና የሚዘገንን መሆኑን ታሪክን መለስ ብላችሁ ብትመለከቱ ትረዱት ነበር። እናንተም አብራችሁ በሃፍረት ሸማ ተከናንባችሁ እንደምትጣሉ ምክራችንን ከአሁኑ እንለግሣለን። እዩኝ እዩኝ እንዳላችሁ ሁሉ ደብቁኝ ደብቁኝ የምትሉበት ጊዜም እሩቅ አይደለም። ማህበራችን የዘረኛው መንግሥት በወገኖቻችን ላይ የሚያደርሰውን ሰቆቃ ለማራዘም በምታደርጉት የትብብርና የባንዳ ተግባራችሁን በቅርብ ይከታተላል፤ በሚቻለን አቅምም እንታገላችኋለን። በመጨረሻው የፍርድ ቀንም ማለትም ሕዝባችን በወያኔና አጋፋሪዎቹ መቃብር ላይ ዲሞክራሲን አስፍኖ በትረ ሥልጣኑን ሲረከብ፤ አሁኑኑ ከዚህ ተግባራችሁ ካልተቆጠባችሁ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በውጭም ሆነ በሀገር ቤት መጋለጣችሁ አይቀሬ ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር